የሰ/መ/ቁ. 21505

2/10/98

ዳኞች፡- አቶ መንበረፀሐይ ታደሰ
አቶ ሐጎስ ወልዱ
አቶ ተገኔ ጌታነህ
አቶ መስፍን እቁበዮናስ
ወ/ት ሒሩት መለሠ

አመልካቾች፡- እነ ወ/ሮ ሉልአደይ ገ/መድኅን /2 ሰዎች/

ተጠሪ፡- አቶ አለማየሁ እሸቴ

<u>ፍ ር ድ</u>

ይህ የሠበር አቤቱታ የቀረበው የሥር ፍ/ቤቶች ሟች አቶ ገዛኸን ጌታቸው ያደረጉት ኑዛዜ በሚበቃ አኳኋን ተጠቃሚውን ወይም ጉዳዩን የሚያመለክት በመሆኑ ፈራሽ ነው፡፡ ነገር ግን የተጠሪ በቤቱ የመኖር መብት ከኑዛዜው ቃል በመነሣት ተረጋግጧል በማለት የሰጡትን ውሣኔ በመቃወም ነው፡፡

ተጠሪ በፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ሟች ወንድማቸው አቶ ገዛኸኝ ጌታቸው በተውት ኑዛዜ በአዲስ አበባ ከተማ ወረዳ 10 ቀበሌ 01 ክልል በሚገኘው የቤ/ቁ 209 በሆነው መኖሪያ ቤታቸው ውስጥ ካለው ሠርቪስ ቤት አንዱን ክፍል እያደሱ እንዲኖሩ የተናዘዙላቸው በመሆኑ የኑዛዜው ወራሽ መሆናቸው ተረጋግጦ ማስረጃ እንዲሰጣቸው ጠይቀዋል፡፡ ፍ/ቤቱም የኑዛዜው ይዘት እርስ በርሱ የሚጋጭና ለአፈፃፀም የሚያስቸግር በመሆኑ ፈራሽ ስለሆነ ተጠሪ የኑዛዜ ወራሽ በመሆናቸው ማስረጃ እንዲሠጣቸው ያቀረቡት ጥያቄ ተቀባይነት የለውም፣ በቤቱ የመኖር መብታቸውን ግን ከኑዛዜው ቃል በመነሣት ፍ/ቤቱ አረጋግጧል በማለት ወስኗል፡፡ የፌዴራል ከፍተኛ ፍ/ቤቱም ይህንኑ ኑዛዜ አጽድቋል፡፡

የአሁኑ የሠበር አቤቱታ የቀረበውም ይህ ውሣኔ የሕግ ስህተት የተፈፀመበት ስለሆነ ሊሻር ይገባዋል በሚል ነው፡፡ ይህ ችሎትም ኑዛዜው ፈራሽ ከሆነ በኋላ የተጠሪን በቤቱ የመኖር መብት በመጠበቅ የሠጠውን ውሣኔ ሕጋዊነት ለመመርመር አቤቱታው ለሠበር እንዲቀርብ በማድረግ የግራ ቀኙን የቃል ክርክር ሠምቷል፡፡

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለኛ ግልባጭ
ፊርማ [signature] ቀን 20/10/98

ከላይ እንደተመለከተው ተጠሪ በሥር ፍ/ቤት ባቀረቡት አቤቱታ ሟች ወንድማቸው በተውት ኑዛዜ ላይ የሟቹ መኖሪያ ቤት አካል በሆነው ሠርቪስ ቤት ውስጥ ቤቱን እያደሱ እንዲኖሩ ስለተናዘዙላቸው የኑዛዜ ወራሽነታቸው እንዲረጋገጥ አመልክተዋል፡፡ ፍ/ቤቶቹም የቀረበላቸውን የኑዛዜ ሰነድ መርምረው የኑዛዜው ቃል ተጠቃሚውን ግልጽ በሆነ ሁኔታ የሚያመለክት እና ኑዛዜው ያረፈበትም ጉዳይ በበቂ ሁኔታ የማያመለክት በመሆኑ፣ በተለይም ደግሞ ከኑዛዜው ቃል ግልጽ አለመሆን የተነሣ በኑዛዜው መሠረት መፈፀም የማይችል በመሆኑ ኑዛዜው ፈራሽ እንዲሆን ወስነዋል፡፡ ተጠሪ ኑዛዜው ፈራሽ ነው ተብሎ በተሰጠው ውሣኔ ላይ ይግባኝ አቅርበው ውሣኔውን አላሻሩም ወይም አላስለወጡም፡፡ ኑዛዜው ፈራሽ መሆኑ ከተወሰነ ደግሞ የኑዛዜ ሠነዱ ዋጋ ወይም ውጤት የለውም ማለት ነው፡፡ ዋጋ በሌለው ወይም ውጤት በሌለው የኑዛዜ ሠነድ መሠረት የተገኘውም መብት በተመሣሣይ ዋጋ አይኖረውም፡፡ ምክንያቱም ለመብቱ መገኘት መሠረት የሆነው የኑዛዜ ሠነድ ራሱ ውጤት አልባ ሆኗልና ነው፡፡ በመሆኑም ፍ/ቤቶቹ ለተጠሪው በቤቱ የመኖር መብት የሰጠው ኑዛዜ ፈራሽ ሆኗል ውጤት የለውም በማለት ከወሰኑ በኋላ በዚህ ፈራሽ በሆነው ኑዛዜ መሠረት የተገኘውን የተጠሪን በቤቱ የመኖር መብት ማረጋገጣቸው እርስ በርሱ የሚቃረን መሆኑን ተረድተናል፡፡ በመሆኑም ሕጋዊ ውጤት በሌለው ሠነድ የተገኘን መብት ሕጋዊ ውጤት እንዲኖረው የተሰጠው ውሣኔ የሕግ ግድፈት ያለበት ነው፡፡

## ው ሣ ኔ

1. የፌ/መ/ደረጃ ፍ/ቤት በመ/ቁ 3196/89 በ3/2/93 እንዲሁም የፌ/ከፍተኛ ፍ/ቤት በመ/ቁ 04129 በ26/11/97 የሰጡት ውሣኔ ተሽሯል፡፡
2. ሟች አቶ ገዛኸኝ ጌታቸው የተውት ኑዛዜ ፈራሽ በመሆኑ ተጠሪ በሰርቪስ ቤቱ እንዲኖሩ በኑዛዜው የተሰጣቸው መብት ሕጋዊ ውጤት የለውም፡፡ በመሆኑም የተጠሪ ክስ ተቀባይነት የለውም፡፡
3. ወጪና ኪሣራ ግራ ቀኙ ይቻቻሉ፡፡

የማይነበብ የአምስት ዳኞች ፊርማ አለበት፡፡

ነ/ዓ

ፌዴራል ጠቅላይ ፍርድ ቤት
ትክክለ ግልባጭ
ፊርማ ___ ቀን 20/10/98